***የዕብዶች የእልቂት ነጋሪት ጕሰማ የነፃነት ትግሉን አንዲት ጋት ወደ ኋላ አያስቀረውም***

***የሚበታተነው ወያኔ እንጂ ኢትዮጵያ አይደለችም***

***ጥሪ ለውሉደ ጽዮን***

(ከይኄይስ እውነቱ)

ኢትዮጵያ በድቡሽት ላይ የተመሠረተች አገር አይደለችም፡፡ ሕዝቧም በዘመናት የአብሮ መኖር መስተጋብር በመዋለድ፣ በባህል መወራረስ፣ በእምነት፣ በታሪክ፣ በክፉም በደጉም ጊዜ በመተሳሰብ በሦስትዮሽ የተገመደ ጥብቅ ዝምድና/ትስስር ያለው ባለረጅም ታሪክና ነፃ ሕዝብ ነው፡፡ ፈተና ለሕዝባችን እንግዳ አይደለም፡፡ ህልውናዋ በባዕዳን ኃይሎች ብዙ ጊዜ አደጋ ላይ ወድቋል፡፡ የውስጥም ከሀዲዎችና የሥልጣን ሱሰኞች ፈትነዋታል፡፡ ሕዝቡንም ለማያባራ እንክርትና እንግልት ዳርገውታል፡፡ በጎ እሤቶቻችን የጋራ እንደሆኑ ሁሉ መከራና ስቃዩም የጋራ ሆኖ ነው የዘለቀው፡፡ ለአንድነቷ ውበት የሰጧት ኅሣዎቿ መጠኑ ይለያይ ካልሆነ በስተቀር በተለያየ ጊዜ በተነሱ አምባገነን አገዛዞች ተረግጠዋል፡፡

የወያኔን አገዛዝ ልዩ የሚያደርገው እንደ ባዕዳኑ በህልውናዋ ላይ የመጣ፣ አገሪቱን በጎሣ/ቋንቋ አጥር ከልሎ ጎሠኝነትን ያስፋፋ፣ የጥላቻ ፖለቲካን ፖሊሲው ያደረገ፣ ጎሣን/ቋንቋን መሠረት አድርጎ የጅምላ ግድያን የፈጸመ፣ ኢትዮጵያና ሕዝቧን በየትኛውም ታሪኳ ተወዳዳሪ በሌለው ሁኔታ ያዋረደ፣ ለጥፋቷም ሌት ተቀን ተግቶ እየሠራ ያለ፣ ሕዝቧንና መሬቷን የሚፈልገው ለማይጠረቃው ዝርፊያው ብቻ የሆነ፣ ጭካኔው ጾስ የሌለው፣ ከትግራይ ምድር በመብቀሉ ብቻ በኢትዮጵያዊነቱ የሚኮራውን የትግራይ ሕዝብ መያዣና ምድሩንም መደበቂያ ዋሻ ያደረገ፣ በባሕርይውም ‹መንግሥት› የሚለውን ታላቅ ስም ለመሸከም በየትኛውም መመዘኛ ብቁ ያልሆነ ተራ የዘረኞችና የወሮበሎች ቡድን መሆኑ ነው፡፡

ይህ የወንበዴዎች ቡድን ማናቸውንም የሕዝብ ጥያቄዎች ለመስማት፣ ለማዳመጥ፣ አዳምጦም ተገቢውን መልስ ለመስጠት ፍላጎቱም ብቃቱም እንደሌለው ከበቂ በላይ አሳይቷል፡፡ ስለሆነም በየትኛውም የኢትዮጵያ ማዕዘን ከዜጎች የሚነሱ ቅሬታዎች በዚህ ሥርዓት ማዕቀፍ ውስጥ መፍትሄ እንደማያገኙ ተረድቶ ሕዝባዊውን ዓመፃ በማቀናጀት አገራዊ (ሥር ነቀል የሥርዓት ለውጥ) ማድረግ ያስፈልጋል፡፡ በአሁኑ ጊዜ በዚህ ወንበዴ ቡድን የሚመራው ሥርዓት መወገድ እንዳለበት ከወያኔና ግብር አበሮቹ በስተቀር በሁሉም ኢትዮጵያውያን ዘንድ ስምምነት አለ፡፡

ይህ ሲሆን ግን በእኔ እምነት ሕዝባችን ሦስት መሠረታዊ ፈተናዎች ከፊቱ ተደቅነዋል፡፡

1ኛ/ በቀቢፀ ተስፋ ገደል አፋፍ ላይ ሆነው የመጨረሻዋን የህልውና ክር ለመያዝ የሚታገሉት እውራነ ልብ የወያኔ አለቆች የተበጠሰ የዕድሜአቸውን ሠንሠለት ለመቀጠል ለግል ጥቅማቸው በተቆጣጠሩት የሕዝብ የብዙኃን መገናኛ አንዴ ሩዋንዳን፣ አንዴ ዩጎዝላቪያን እያነሱ፤የትግራይን ሕዝብ መያዣ ለማድረግ እና ከቀሩት ኢትዮጵያዊ ወገኖቹ ጋር ማለቂያ ወደሌለው የርስበርስ ግጭት ውስጥ እንዲገባ የእልቂት/የጥፋት ነጋሪት እየጐሰሙ መሆናቸው፤

በእውነቱ ይህ ሥጋት መሠረት የለውም  አንልም። እብዶቹ የወያኔ አለቆች ፍላጎታቸውንና ከልባቸው ሞልቶ የተረፈውን ነው አደባባይ ወጥተው የለፈፉት። አገሩን የሚወድ ዜጋ ኹሉ በእጅጉ ያሳስበዋል። ይሁን እንጂ የነዚህ ድኩማን አእምሮ በፈጠረው የእልቂት ድግስና ሥጋት ምክንያት የኢትዮጵያ ሕዝብ ዕድሜ ልኩን ለወያኔ በባርነት የሚገዛበት ሁኔታ አይኖርም። የግጭቱ ምንጭ ሥልጣኑንና የዘረፈውን የኢትዮጵያ ሀብት በትግራይ ልጆች ደም ለመጠበቅ እልቂት የሚያውጀው ወያኔ መሆኑን ከተረዳህ ይህ ሥጋት መሠረት እንዳይኖረው ብቸኛው መፍትሔ  የትግራይ ሕዝብ ኢትዮጵያዊነቱን ወያኔ እንዳይነጥቀው እምቢ በማለት ከቀረው ኢትዮጵያዊ ወገኑ ጋር ወያኔን ለማስወገድ የሚደረገውን ትግል ሳይውል ሳያድር በተግባር መቀላቀል ነው። ጥቃት የሚመጣ ከሆነ እልቂትን ከሚያቅራራው ወያኔ እንጂ ከወገንህ ኢትዮጵያው አይሆንም። ወያኔ ይህንን ለማድረግ ወደ ኋላ የማይል መሠሪ ኃይል መሆኑን አንተም በሚገባ ታውቀዋለህና። ሀብትና ብልጽግና የአገር ህልውናና የሕዝብ አንድነት ከተጠበቀ በኋላ ውሎ አድሮ በላባችን እናመጣዋለን። በእኩልነት ላይ የተመሠረተ ሥርዓት ከገነባን ኢትዮጵያ የምትሰጠን በረከት ለሁላችን በቂ ነው። በመሆኑም ይህ ጥሪ በወያኔ ዝርፊያ ተጠቃሚ የሆኑትን የትግራይ ተወላጆች ጭምር ይመለከታል። ኢትዮጵያዊው የትግራይ ወገኔ ሀብትህና ዋስትናህ የኢትዮጵያ ሕዝብ ፍቅር እንጂ አላፊ ጠፊው ወርቅና ብር አይደለም። ወያኔ ከሠላሳ ዓመታት በላይ በስምህ የነገደብህ ይበቃል። ከኢትዮጵያውያን ወገኖችህ ሊያቆራርጥህ ባዘጋጀልህ ወጥመድ ላለመግባት ዛሬውኑ ወስነህ በአራቱም ማዕዘናት ከሚገኙ ወገኖችህ ጋር እጅ ለእጅ ተያያዝ። ባንዶችና ከሐዲዎችን እምቢኝ አሻፈረኝ ብለህ አሳፍራቸው። ይህን እንደምታደርግ ጽኑ ተስፋ አለኝ። የኢትዮጵያ መኩሪያ የጽዮን ልጅ ነህና። ይህንንም ተስፋ መሠረት በማድረግ ነው የሚበታተነው ወያኔ እንጂ ኢትዮጵያ አይደለችም የምለው።

*ለተቀረው ኢትዮጵያዊ ወገኔ የማስተላልፈው መልእክት፤*

የትግራይ ሕዝብ በሥጋና በደም የተዋሐደህ ዘመድህ ነው። መቼም ጠላትህ ሆኖ አያውቅም። ከጉያው የበቀሉ የታሪክ እንክርዳዶችን (ወያኔን) ስትነቅል ስንዴውንና ኢትዮጵያውን የትግራይ ሕዝብ እንዳትነካ ጥብቅ ጥንቃቄ አድርግ። ዋስትና ሁነው። ይህንንም በተግባር አሳየው። በምንናገረውና በምንጽፈው ኹሉ ማኅበራዊውን የብዙኃን መገናኛ ኃላፊነት በተሞላበት ሁኔታ እንጠቀምበት። ኅሊና ቢሶች የሆኑት የወያኔ የጦር አበጋዞች ለሚለፍፉት የእልቂት ወሬ የገደል ማሚቶ አንሁን።

2ኛ/ ይህ አጥፊ ቡድን መሠረቱ የተናጋ ቢሆንም ከእስካሁኑ የከፋ ጥፋት ሳይደርስ እንዴት ይወገድ፣ ማን ያስወግደው የሚለው ነው፤

እንደሚታወቀው ሕዝቡ በተለያዩ አካባቢዎች ራሱን በራሱ አደራጅቶ የጎበዝ አለቃ መርጦ መራራውን ትግል ከጀመረ ውሎ አድሯል። ይህንን እውን ለማድረግ የሕፃናት ደም ጭምር እየተገበረ ነው። ይህንን መልእክት በምጽፍበት ሰዓት በዚሁ ጨካኝ ሥርዓት ውስጥ ተወልደው ያደጉ ጨቅላ ወጣቶች የማይተካውን የሕይወት መሥዋዕትነት እየከፈሉ ይገኛሉ። በየቦታው በተበታተነ መልኩ የምናደርገው የሕዝባዊ እምቢተኝነት እንቅስቃሴ የበሽታው መገለጫ የሆኑ ልዩ ልዩ ምልክቶች ላይ ማተኮር የለበትም። ጥያቄው የሥርዓት ለውጥ በመሆኑ መፍትሄው

ነቀርሳውን (ወያኔን) ከሥሩ ነቅለን ማስወገድ ብቻ ነው ። ለነፃነት የሚደረገው ትግል ለመገለጫዎቹ (የማንነት፣ የመሬት፣ ራስን በራስ የማስተዳደር ጥያቄዎች ወዘተረፈ) መልስን ይሰጣልና። ትግሉን በምልክቶቹ ዙሪያ ማድረግ ተጠቃሚ የሚያደርገው 24/7 ተንኮል የሚሸርበውን ወያኔ ብቻ ነው።

*በአገር ውስጥም ሆነ በውጭ የምትገኙ የተቃዋሚ ‹ፖለቲካ ማኅበራት› ወይም ቡድኖች ሚና*

የጥፋት ነጋሪት የሚጎስሙት ጉዶች ለዕኩይ ተግባር 24/7 ሲሠሩ እኛ ለነፃነቱ ከሚዋደቀው ሕዝብ ጋር ለይስሙላ ቆመናል የምንል በአገር ውስጥም ሆነ በውጩ ዓለም የምንገኝ የተቃዋሚ ‹ፖለቲካ ማኅበራት› ከመግለጫ ማውጣት ባለፈ ምን እያደረግን ነው? የወያኔን ህልውና ለመጠበቅ ባሠለጠኑት አውሬ (አጋአዚ ጦር) የነገ አገር ተረካቢ ወጣቶች እየከፈሉ ያሉትን መሥዋዕትነትና የኢትዮጵያ እናቶች መሪር ሐዘን ከልብ የሚሰማን ከሆነ ቢያንስ ሕዝባዊ ትግሉን በሁለት መልኩ ማገዝ እንችላለን፤

ሀ/ ልዩነታችሁ እንደተጠበቀ ሆኖ ወያኔን የማስወገዱ ጉዳይ የጋራ አጀንዳችሁ በመሆኑ በዚህ ዙሪያ ጊዜ ሳትሰጡ ኅብረት መፍጠር፤ በዚህ መታመናችሁን ለሕዝብ ካሳያችሁ በወያኔ ውድቀት ለሚመሠረተው አዲስ ሥርዓት ሕዝብ ተስፋ እንዲጥልባችሁ መሠረት ይሆናል።

ለ/ ላለፉት 25 ዓመታት የጎሣ/ቋንቋ ፌዴራሊዝም፣ የጎሣ ፖለቲካ በአገራችን ያስከተለውን ጥፋት በሕዝባችን ላይ ያደረሰውን አለመተማመንና እልቂት እንኳን ፖለቲካን ዋና ሙያችሁ ያደረጋችሁና በፖለቲካ ማኅበር ተደራጅታችሁ የአንድ ጎሣ የበላይነትን የሚያረጋግጥና ሕዝባችንን እኩል ተጠቃሚ የማያደርግ ሥርዓት ለአንዴና ለመጨረሻ ጊዜ እንዲወገድ እንታገላለን የምትሉ ኃይሎች ይቅርና ገጠሬው ኢትዮጵያዊ (እውነቱን ለመናገር ቀድሞአችኋል) ጠንቅቆ ያወቀው ጉዳይ ነው።

ስለሆነም የለውጥ ኃይል ለመሆን እናንተ ቅድሚያ መለወጣችሁን ለሕዝብ በተግባር አሳዩ። ይኸውም በየመንደራችሁ የምታቀነቅኑትን የጎሣ ፖለቲካ እርግፍ አድርጋችሁ በመተው ይጀምራል። በራሳችሁ (ዓላማ፣ ፕሮግራም፣ ፖሊሲ፣ አማራጭ አስተሳሰብ ወዘተረፈ) የምትተማኑ ከሆነ እንደ ወያኔ በጎሣ ጉያ ሥር መወሸቅ አያስፈልግም። በእኔ እምነት የጎሣ ፓርቲ ውክልናው ትንሽም ይሆን ትልቅ፣ መሪዎቹ የፈለገውን ያህል ቅንና በጎ አሳቢ ቢሆኑ የምንመኘውን በእኩልነት ላይ የተመሠረተና የሕግ የበላይነትን የሚያረጋግጥ ሥርዓት ሊያመጣ አይችልም። ሌላ የጭቆናና የዝርፊያ አዙሪት ውስጥ የሚከተን እንጂ።

በቅርቡ በአማርኛና ኦሮምኛ ቋንቋ ተናጋሪ ኢትዮጵያውያን መካከል የተፈጠረው ጅምር ኅብረትና አንድነት የበለጠ ሊጠናከር፣ለዚህም ተግቶ መሥራት ያስፈልጋል። ከሚሸፍኑት የሕዝብ ብዛት አንፃር ለአገር አንድነትና ለግዛት ሉዐላዊነት ለተቀሩት ኢትዮጵያውያን ሁሉ በጎ አብነት ይሆናልና።

በሌላ በኩል ለኦሮሞ ወገኖቻችን ጥብቅና ቆመናል የሚሉ አንዳንድ ቡድኖች/ግለሰቦች እና ማኅበራዊ ሚዲያዎች ደጋግመው *‹‹ኦሮሞ እና የኢትዮጵያ ሕዝቦች››* የሚል ንግግር

ሲያስተላልፉ ይደመጣሉ። የዚህ አባባል አንድምታ ምንድን ነው? ግንዱ ኦሮሞ ኢትዮጵያዊ ካልሆነ ምን ይሁን? እነዚህ ወገኖች ጎሣን የሚያስቀድም ፖሊሲ ቢኖራቸው እንኳን ‹ኦሮሞ ኢትዮጵያውያን› ማለቱ የሚከብድ አይመስለኝም። አለበለዚያ አጥብቀን ከምንቃወመው ወያኔ የሚያመሳስለን አይሆንም ወይ? ጀግናው ወንድማችን ፈይሳ ሌሊሳ ለምን ምሳሌ አይሆነንም?

## *የአገር መከላከያ ሠራዊት ሚና*

ወያኔ ህልውናውን ያንጠለጠለው እንደ ክፉ ውሻ ደም እያጠጣ ባሳደገው አጋአዚ በሚባለው ጨካኝ ጦሩና የሕዝብና የአገር ሳይሆን የወያኔን አለቆችና የገነቡት የዘርፊያ ሥርዓት ለመጠበቅ ባደራጀው ደኅንነቱ ላይ ነው። እነዚህ ኃይሎች ከአፈጣጠራቸው በራሳቸው አእምሮ እንዳያስቡ ተደርገው የተደራጁ በመሆናቸው ከጥፋታቸው ይመለሳሉ የሚል ተስፋ ባይኖረንም ከውስጣቸው ጥፍጣፊ ኅሊና ያለው ካለ ቢያንስ ንጹሐን ኢትዮጵያውያንን መግደል ማቆሚያው ጊዜ አሁን ነው።

በአንፃሩም ወያኔ የአገር መከላከያ ሠራዊትን ለራሱ ጠባብ ጥቅም ያደራጀውና ከላይ እስከ ታች በራሱ የጎሣ መኮንኖች ተብትቦ የያዘው ቢሆንም፣ ሕዝባዊ ትግሉን ከፍጻሜ ለማድረስ ወሳኝ ሚና አለው። ይኸውም በጅምር ደረጃ እንደታየው የሕዝብ ጠላት የሆነውን ወያኔ እምቢ በማለት ሕዝባዊነቱንና በእውነት የአገር መከላከያ መሆኑን ከሕዝብ ጋር በመሰለፍ በተግባር ማሳየት አንዱ ሲሆን፤ ይህን ማድረግ የማይችሉ ደግሞ ቢያንስ ወገኖቹ ላይ ከመተኮስ መታቀብ ይኖርበታል። ይህንን ማድረግ ከቻለ የኢትዮጵያ ሕዝብ ባለውለታ ይሆናል። በሚገነባው አዲስ ሥርዓት ውስጥ የአገር መከላከያ ሠራዊት ሆኖ እንዲቀጥል ዋስትናው ወገኑ የኢትዮጵያ ሕዝብ ይሆናል።

3ኛ/ ወያኔ ከተወገደ በኋላ ኢትዮጵያውያን (በዘር፣በጎሣ፣ በሃይማኖት፣በፆታ፣ ወዘተረፈ ልዩነት ሳይደረግባቸው) በእኩልነት የሚታዩበት፣ ነፃነታቸውና መብታቸው የሚከበርበት፣ አገሪቱ በምትሰጠው ሀብትና ዕድል በጋራ ተጠቃሚ የሚሆኑበት፣ ***ጎሣን መሠረት ያላደረገና*** የሕግ የበላይነት የሠፈነበት ሥርዓት ለመገንባት ምን ዋስትና አለ፤

የዚህ አስተያየት አቅራቢ የወያኔን ሥርዓት በምን መልክ እናስወግደዋለን ከሚለው ጥያቄ ባልተናነሰ የዘረኛው አገዛዝ መውደቅን  ተከትሎ የሚመሠረተው ሥርዓት እንዴትና በማን የሚለውም እጅግ ያሳስበዋል።

በዚህ ረገድ ጥቂት ምሁራን አማራጮችን ለማቅረብ ጥረት እያደረጉ ቢሆንም በቂ ነው የሚል እምነት የለኝም። ሰሞኑን በታላቁ ኢትዮጵያዊ ምሁር በጋሼ መሥፍን የቀረበውን ጨምሮ ለዘለቄታው የሚያገለግሉ አማራጮችን ጊዜ ሳይሰጡ ለሕዝብ ማቅረብ ከምሁራኑ ይጠበቃል፤ ሕዝብ፣ ተቃዋሚ የፖለቲካ ማኅበራት፣ የሲቪክ ማኅበራት፣ የአገር ሽማግሌዎች፣ ታዋቂ ግለሰቦች፣ ወዘተ እንዲተቹትና እንዲመክሩበት ማድረግ ያስፈልጋል።

በመጨረሻም በአገራችን እየታየ ያለው የለውጥ ማዕበል በየዕለቱና ሰዓቱ ተለዋዋጭ በመሆኑ (ነገሮች ከቍጥጥር ውጭ ሳይሆኑ) ከፍ ብዬ በሦስት ዐበይት ርእሶች ያቀረብኩት አስተያየት አጣዳፊ ውሳኔዎችን የሚሹ (time is the essence) መሆኑ ለማስገንዘብ እውዳለሁ፡፡

የኢትዮጵያ አምላክ የእልቂትን ወሬ ያርቅልን፡፡ በጠብና ጥላቻ ምትክ እርቅና ፍቅርን ያንግሥልን፡፡